# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን

## የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ እና ክዋኔ ኦዲት መመሪያ

ቁጥር ----/2014

መጋቢት 2014

አዲስ አበባ

## መግቢያ

የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ማንኛውም የልማት ሀሳብ ንድፍ ሲዘጋጅ፣ ቦታው ሲመረጥ ወይም ሲገነባ እንዲሁም በመተግበር ላይ ያለ እንቅስቃሴ ሲሻሻል ወይም ሲቋረጥ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ በመተንበይና አስቀድሞ በመመርመር በውል የታሰበበትን ልማት ለማምጣት የሚያግዝ በመሆኑ፤ በማህበራዊና በተፈትሮአዊ አካባቢ ላይ ጉልህ አሉታዊ የአካባቢ ተፅዕኖ ያደርሳሉ ተብለው ለሚገመቱ የማህበራዊና የልማት ፕሮጀክቶች ስራው ከመጀመሩ በፊት በማህበረሰባዊና በተፈጥሮአዊ አካባቢ ላይ የሚያስከትለውን አሉታዊ የአካባቢ ተጽዕኖ ለመቀነስና ለማገድ በቅድሚያ መርምሮ ማረጋገጥ አሰፈላጊ በመሆኑ፤ በአስተዳደሩ ውስጥ የሚካሄዱ የልማት እንቅስቃሴዎች የአካባቢ ደህንነትን ሳያናጉና ከዘላቂ ልማት መርህ ጋር በተሰማማ ሁኔታ ተፈጻሚ መሆናቸውን መከታተልና ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ አስተዳደራዊ ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲኖር ለማድረግ በአጠቃላይ እራሱንና አካባቢውን በሚመለከቱ የልማት እቅዶችን አወጣጥና ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ህዝቡን በተለይ ለማሳተፍ አስፈላጊ በመሆኑ ለዚህም የአፈጻጸም መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 74/2014 አንቀፅ 48 በተሰጠው ስልጣን እና የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ደንብ ቁጥር 21/1998ን መሠረት አድርጎ ይህ የአፈጻጸም መመሪያ ተዘጋጅቷል::

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩ <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማና ክዋኔ ኦዲት መመሪያ ቁጥር ---- ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### ፪ <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ፡-

፩ "አካባቢ" ማለት በመሬት፣ በአካባቢ ዓየር፣ በዓየር ሁኔታና በዓየር ንብረት፣ በውኃ፣ በህያዋን፣ በድምፅ፣ በሽታ፣ በጣዕም፣ በማህበራዊ ጉዮች፣እና በስነ-ህይወት ሳይወሰን በተፈጠሮአዊ ሁኔታዎች ወይም በሰው አማካኝነት ተሸሽለው ወይም ተለጠው የሚገኙ ነገሮች በሙሉና ያሉበት ቦታ እንዲሁም መጠናቸው ወይም ሁኔታቸው ወይም ደግሞ የሰው ወይም የሌሎች ህያዋን ሁኔታን የሚነኩ መስተጋብሮቻቸው ድምር ነው።

፪ "ተፅዕኖ" ማለት በአካባቢ ወይም በሌሎች ንዑሳን ክፍሎች ላይ በሚፈጠር ለውጥ ምክንያት ማንኛው በአካባቢያዊ፣ ማህበራዊና፣ ኢኮኖሚዊ ወይም ባህላዊ ገፅታዎች ላይ የሚከሰት ተከታይ ለውጥ ነው።

፫ "የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ" ማለት አንድ ፕሮጀክት የሚያስከትለውን አወንታዊም ሆነ አሉታዊ ውጤት በቅድሚያ ማወቂያ ዘዴ ነው።

፬ "የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ሰነድ " ማለት በፕሮጀክቱ ባለቤቶች ለማህበርዊና አካባቢያዊ ደህንነት ሲባል የሚወሰዱ እርምጃዎችን አስመልክቶ ለባለስልጣኑ የሚቀርብ የጥናት ሰነድ ነው፡፡

፭ "ፕሮጀክት" ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት ማንኛውም አዲስ የልማት እንቅስቃሴ ወይም በነባር ድርጅት ላይ የሚደረግ ጉልህ መስፋፋት ወይም ለውጥ ወይም ደግሞ ተቋርጦ የነበረ ስራን መልሶ ለመጀመር የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው፡፡

፮ "የፕሮጀክት ባለቤት" ማለት ፕሮጀክቱ በመንግስት የተወጠነ ሲሆን የሚመለከተው የመንግስት አካል ወይም በግሉ ዘርፍ የተወጠነ ሲሆን ባለሀብት የሆነው ሰው ነው፡፡

፯ "ማስፋፋት፣ መለወጥ ወይም ማሻሻል" ማለት የነባር ድርጅትን የሙሉ አቅም ምርት ወይም አገልግሎት ወይም ተግባራዊ ያልሆነ ጥናትን ከሃያ አምስት በመቶ በላይ በእሴት ማሳደግ ሲሆን ይህም በዓይነት፣ በጥራት፣ በመጠን ወይም በሁሉም መጨመርን የሚያጠቃልል ነው፡፡

፰ "የመንግስት ሰነድ" ማለት ፖሊሲ፣ ስልት፣ መርህ፣ ግብር፣ ህግ ወይም የዓለም ዓቀፍ ስምምነት ነው፡፡

፱ "አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፡፡

፲. "ፈቃድ ሰጪ መስሪያ ቤት" ማለት እንደሁኔታው የኢንቨስትመንት፣ የንግድ፣ ወይም የሌላ ስራ ፈቃድ ለመስጠት በህግ ሥልጣን የተሰጠው ማንኛውም የመንግስት አካል ነው፡፡

፲፩. "ባለሥልጣን" ማለት የአዲስ አባበ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን እና በክፍለ ከተማ ደረጃ የተቋቋሙ የአካባቢ ጥበቃ ጽ/ቤቶችን ነው፡፡

፲፪. "ድርጅት" ማለት በንግድ ህግ መሰረት ወይም በሌሎች ህጎች የተቋቋመና በንግድ ሥራ ላይ የተሰማራ የማምረቻ ወይም ማከፋፈያ ወይም የአገልግሎት መስጫ ተቋም ነው፡፡

፲፫. "ነባር ተቋም" ማለት በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሂደት ያላለፈና በስራ ላይ የሚገኝ የማምረቻ ወይም የአገልግሎት መስጪያ ተቋም ነው

፲፬. "ክዋኔ ኦዲት" ማለት በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሰነድ አቅርቦና በሂደቱ አልፎ የጸደቀ ፕሮጀክት በትግበራው ወቅት ባቀረበው ሰነድ መሠረት እየተከናወነ መሆኑን የማረጋገጥ ሥራ ነው፡፡

፲፭. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

፲፮. "የመጀመሪያ ደረጃ ወይም ከፊል የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ" ማለት አሉታዊ ተፅዕኖ ያደርሳሉ ተብለው ለተገመቱ ፕሮጀክቶች የሚካሄድ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ነው፡፡

፲፯. "ሙሉ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ" ማለት የጎላ አሉታዊ ተፅዕኖ ያደርሳሉ ተብለው ለተገመቱ ፕሮጀክቶች የሚካሄድ ጥልቅና ሰፊ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ነው፡፡

## ፫ <u>የጾታ አገባቡ</u>

በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

## ፬ የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ደንብ መንግስታዊ፣ መንግስታዊ ባልሆኑና በግል ባለሀብቶች በሚቀርቡ የልማት ፕሮጀክቶች፣ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ደንቡ ከመጽናቱ በፊት የጸደቁ ፕሮክቶች ወይም የተቋቋሙ ድርጅቶች የማስፋፊያ ተጨማሪ ስራ ካከናወኑ ወይም ሥራቸውን ከለወጡ ወይም ሥራ አቋርጠው እንደገና ከጀመሩ ወይም በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሂደት ባለማለፋቸው የአካባቢ አያያዝ ዕቅድ እንዲያቀርቡ በሚጠየቁት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ፭ ዓላማ

የመመሪያው ዓላማ በአዲስ አበባ ከተማ ላይ እየደረሰ ያለውን የአካባቢ መበከልና መጎሳቆል ለመቀነስ አዳዲስ የሚታቀዱ ፕሮጀክቶች በአካባቢ ላይ ሊያደርሱ የሚችሉትን አሉታዊ ተፅዕኖ አስቀድሞ ለመከላከል የወጡ አዋጆችና ደንቦችን ለማስፈጸም ነው፡፡

## ፮ የህግ ማዕቀፎችና አስተዳደራዊ መዋቅሮች

፩ በፌደራል መንግስት የጸደቁ አዋጆችና ደንቦች

ሀ. የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299/1995

ለ. የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 300/1995

ሐ. የኢንዱስትሪ ብክለት መከላከያ የሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 159/2001

፪ የአዲስ አአበባ ከተማ አስተዳደር የጸደቁ አዋጅና ደንቦች

ሀ. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 74/2014

ለ. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ደንብ ቁጥር 21/1998

# ክፍል ሁለት
# የፕሮጀክቱ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሂደት መስፈርቶች

## ፯ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ስለሚያስፈልጋቸው ፕሮጀክቶች

፩ በዚህ መመሪያ መሰረት

ሀ. በአካባቢ ላይ የሚደርሱት ተፅዕኖ የለም ወይም የጎላ ተፅዕኖ አያደርሱም ተብለው የሚታሰቡ ፕሮጀክቶችን ዝርዝር

ለ. አሉታዊ ተፅዕኖ ያደርሳሉ ተብለው የሚታሰቡትንና የመጀመሪያ ደረጃ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የሚያስፈልጋችውን ፕሮጀክቶች ዝርዝር እና

ሐ. አሉታዊ ተፅዕኖ ያደርሳሉ ተብለው የሚታሰቡትንና ሙሉ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የሚያስፈልቸውን ፕሮጀክቶችን ዝርዝር (ፌደራል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤት በተለየው መሠረት) ከዚህ ሰነድ ጋር ተያይዟል፡፡

፪ በዚህ መመሪያ ያልተካተቱ ፕሮጀክቶች ሲያጋጥሙ በየትኛው ዘርፍ ውስጥ እንደሚወድቁ ባለሥልጣኑ ይወስናል፡፡

፫ በዝርዝሩ ውስጥ በፌደራል ደረጃ የጎላ ተፅዕኖ የላቸውም የተባሉ ፕሮጀክቶች በከተማ መሃል ወይም የህዝብ ጥግግት ባለበት አካባቢ ተፅዕኗቸው የጎላ ሊሆን ስለሚችል ሙሉ የአካባቢ ተፅዕኖ እንዲደረግባቸው ሊወሰን ይችላል።

## ፰ የግምገማ ሂደትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች

፩ በዚህ መመሪያ መሰረት በአካባቢ ተፅዕኖ ሥር ማለፍ የሚገባቸው ፕሮጀክቶች ከባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ሳያገኙ ሥራ አይጀምሩም።

፪ ማንኛውም ፈቃድ ሰጪ መስሪያ ቤት የኢንቨስትመንት፣ የንግድ፣ ወይም ሌላ ሥራ ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት ፕሮጀክቱ ተግባራዊ እንዲሆን ከባለሥልጣኑ ይሁንታ መሰጠቱን ማረጋገጥ አለበት።

፫ በዚህ መመሪያ መሰረት በተለያዩ እርከኖች የሚካሄድ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የሚያስከትለው ወጪ በፕሮጀክቱ ባለቤት ይሸፈናል።

፬ በዚህ መመሪያ መሰረት በባለሥልጣኑ የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ በአካባቢ ተፅዕኖ ምክንያት በሚደርስ ጉዳት የፕሮጀክቱን ባለቤት ከተጠያቂነትና ከሃላፊነት ነፃ አያደርገውም።

## ፱ የተፅዕኖ መወሰኛ ታሳቢዎች

፩ ጉልህ የአካባቢ ተፅዕኖ ያስከትላሉ ተብለው የሚታሰቡ ፕሮጀክቶችን ዝርዝር ከዚህ መመሪያ ጋር በአባሪነት ተያይዘዋል።

፪ የፕሮጀክቶች ጉልህ ተፅዕኖ ሲባል ታሳቢ የሚያደርገው

- ለጉዳት የሚጋለጠውን ህዝብ ብዛት
- የሚከተለው የጉዳት ዓይነት
- ለጉዳት ከሚጋለጠው ክፍለ አካባቢዎች
- የተፅዕኖው /ጉዳቱ/ የቆይታ ጊዜ
- በአጭርና በረጅም ጊዜ በስፍራው የሚታቀዱ የልማት እንቅስቃሴዎች የሚያስከትሉትን ድምር ተፅዕኖ
- የሚከተለውን ተፅዕኖ ለመቋቋም የሚቻል ወይም የማይቻል ስለመሆኑ
- የልማት እንቅስቃሴውን ተከትለው ከሚፈጠሩ ተፅዕኖዎች እና ከሌሎች ተፈላጊ ሁኔታዎች አኳያ ይወሰናል።

## ፲. ጉልህ ተፅዕኖን በተመለከተ

ፕሮጀክቱ ጉልህ ተፅዕኖ ያስከትላል የሚባለው

- በሰውና በእንስሳት ጤናና ህይወት ላይ ጉዳት የሚያደርስ ከሆነ
- በአካባቢ ሥነ-ምህዳር ላይ ጉዳት የሚደርስ ከሆነና ጉዳቱ ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው ይልቅ በልጦ ከተገኘ
- አደገኛ ቆሻሻ ውጋጅ የሚለቅ ከሆነ
- ጨረርና ሙቀት ወደ አካባቢ የሚለቅ ከሆነ
- በማንኛውም መስፈርት የአካባቢን ደረጃ ተላልፎ በአየር፣ በውኃና በአፈር ላይ ብክለት የሚያደርስ ሆኖ ከተገኘ

## ፲፩. የተፅዕኖ ግምገማ ሂደት

በዚህ መመሪያ መሰረት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሂደት በቅደም ተከተል ማሟላት ያለበት

፩ ቀዳሚ ምርመራና ማጣሪያ (prescreening)

ባለፕሮጀክቱ ወይም ህጋዊ ወኪሉ በቅደሚያ በአካል በመቅረብ የታሰበውን ፕሮጀክት ምንነት ባህርይና ቦታ በመግለፅ በህግ ስልጣን ከተሰጠው የአካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት ፕሮጀክቱ መተግበር እንዲችል አስተያየት እንዲሰጥበት በጽሁፍ ማመልከቻ ይጠይቃል:: ባለሥልጣኑ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የሚመለከታቸውን መንግሥታዊ መሥሪያ ቤቶችን፣ ባለድርሻ አካላትን፣ ለችግሩ ተጋላጭ የሆኑና ሌሎች ፍላጎቱ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎችን ሊያወያይና ሃሳባቸውን ሊቀበል ይችላል።

ሀ. ማንኛውም ባለፕሮጀክት ጥናቱን ከማስጠናቱ በፊት ከአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን መ/ቤት ጋር መመካከር አለበት

ለ. ምክክሩ ባለፕሮጀክቱ ወይም ህጋዊ ተወካዩ ከባለሥልጣኑ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ጋር ይሆናል።

ሐ. በምክክሩ ወቅት ባለፕሮጀክቱ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሰነድ ማስጠናት ይኖርበት እንደሆነ፣ በየትኛው የባለሥልጣኑ እርከን ደረጃ ማቅረብ እንዳለበት ይገለጽለታል።

መ. ባለፕሮጀክቱ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ማስጠናት ካለበት ህጋዊ አማካሪዎችን ከተዘጋጀው ዝርዝር በራሱ እንዲመርጥ ይደረጋል። ከዚህ ውጭ የሚካሄድ የአማካሪ ጥቆማ አመራረጥ ተቀባይነት የለውም።

ሠ. ምክክሩ የተካሄደለት ባለፕሮጀክት ስለምክክሩ ሂደትና ስለፕሮጀክቱ ይዘት መረጃ ይያዛል

፪ የጥናቱን ሁኔታ መለየት (screening)

ሀ. ባለፕሮጀክቱ ወይም ህጋዊ ወኪሉ በህግ ስልጣን ከተሰጠው የአካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት በአካል በመቅረብ ስለታሰበው

- ፕሮጀክት ምንነት፣
- ስለሚጠቀመው ጥሬ ዕቃና ማሽነሪ ፣
- ስለማምረት/ አገልግሎት ስራው ሂደት፣
- በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ይከሰታሉ ተብለው ስለሚገመቱ አወንታዊና አሉታዊ የአካባቢ ተፅዕኖዎች ባህርያትና የቆይታ ጊዜ፣
- ስለሚጠቀመው የሀይል ምንጭና ፍጆታ፣
- ስለሚወስደው ቦታ ስፋት፣
- ስለውጋጅ አይነትና ባህርይ፣
- ስለቦታው የመሬት አጠቃቀም ፕላንና የወደፊት የልማት እንቅስቃሴ፣
- በአቅራቢያ ስለሚገኙ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ቅርሶችና ሀብቶች፣
- አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ ወይም ለማስወገድ ስለሚወሰድ እርምጃ ወይም ዕቅድ፣
- ስለአካባቢ አያያዝ መርሀግብር፣ ከፕሮጀክቱ ግንባታ እስከ ትግበራና ስራ በማቋረጥ ወቅት

- የውስጥ ክትትልና ቁጥጥር ስልት መዘርጋት ወዘተ----- በዝርዝር መግለጽ ይጠበቅበታል:
- ይህንን የቀረበውን ገለጻ መሰረት በማድረግ የጥናቱን ሁኔታ ለመለየት ያስችላል:: በዚህ መሰረት

ለ. ፕሮጀክቱ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ ማቅረብ የማያስፈልገው ሆኖ ከተገኘ ደንበኛው ወዲያውኑ ይስተናገዳል::

ሐ. በቀረበው ሪፖርት መሰረት በባለሥልጣኑ ባለሙያዎች ፕሮጀክቱ የጎላ ተጽዕኖ አያደርስም ተብሎ ከታመነበት የመጀመሪያ ደረጃ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሰነድ ከተቻለ ባለፕሮጀክቱ ወይም ህጋዊ ወኪሉ ወይም በአማካሪ ድርጅት ተሰርቶ እንዲያቀርብ ይወስናል:: ይህ ውሳኔ በክፍለ ከተሞች ወይም በማዕከል ደረጃ ሊሰጥ ይችላል::

መ. ነገር ግን የታሰበው ፕሮጀክት ሊያስከትል የሚችለው ተጽዕኖ ከፍተኛ ነው ተብሎ ከታመነ ወይም አጠራጣሪ ሁኔታ ካለ ሙሉ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት ሰነድ ፍቃድ በተሰጠው ህጋዊ አማካሪ ድርጀት ተሰርቶ እንዲቀርብ በማዕከል ደረጃ ብቻ ይስተናገዳል::

፫ የጥናቱን ደረጃ መወሰን (scoping)

ከላይ የጥናቱን ደረጃ (scoping) ለመወሰን እንዲያስችል በባለፕሮጀክቱ ወይም በህጋዊ ወኪሉ በኩል የቀረበውን ገለጻ መሰረት በማደረግ በስራ ሂደት ሊፈጠር ስለሚችለው የብክለትና የጉዳት ዓይነት ተጋላጭ ስለሚሆነው አካባቢ፣ ስለጉዳቱ የቆይታ ጊዜና ድንበር ተሻጋሪ መሆን አለመሆኑን እና ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ የሚቻልበት መንገድ መኖር አለመኖሩን ለመረዳት ያስችላል::

ስለሆነም የፕሮጀክቱን ባህርይ በመረዳትና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ ምን ሊመስል እንደሚገባ ለመወሰን ስለሚረዳ ባለፕሮጀክቱ የጥናቱን ደረጃ መወሰኛ ሪፖርት ሊጠየቅ ይችላል።

፬ የቀረበውን ጥናት ሰነድ መመርመር (Evaluating the Report)

በህግ ስልጣን የተሰጠው የአካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤት ባለሙያዎች በክፍለ ከተማ ወይም በማእከል ደረጃ የቀረበውን የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ ጥናት ሰነድ በመመርመር አስፈላጊውን ፎርማሊቲ ማሟላቱንና ፕሮጀክቱ የታሰበበትን ቦታ በአካል በመገኘትና በመመልከት በቀረበው ሰነድ ላይ መካተት ሲገባቸው ያልተካተቱ ጉዳዮችን እንዲካተቱ በማድረግና አላስፈላጊ ጉዳዮችን በማስቀረት ሰነዱ እንዲስተካከል ይሆናል:: ሰነዱ በፌደራል ደረጃ የተዘጋጀውን ጋይድላይን (Review Guideline- content & scope of the report) ይዘት በመከተል መዘጋጀት ይኖርበታል።

የቀረበው የጥናት ሰነድ ሙሉ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ከሆነ የባለሥልጣኑ ባለሙያዎች የቀረበው ሰነድ

ሀ. የጥናቱን አላማ፣ የፕሮጀክቱን አሉታዊና አወንታዊ ተፅዕኖዎች፣

ለ. አስፈላጊ የሆኑ የህግ ማዕቀፎች መጠቀሳቸውን፣ ትክክለኛ የተፅዕኖ መቀነሻ ወይም ማስወገጃ ዘዴዎች መካተታቸውን፣ የአካባቢ አያያዝ እቅድ መካተቱን ፣ በህግ ፍቃድ

በተሰጠው አማካሪ ድርጅት መሰራቱን፣ አስፈላጊ መረጃዎች ሁሉ መካተታቸውን በአቅራቢያ በሚገኙ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ሀብቶች ወይም ቅርሶች ላይ ሊደርስ የሚችል ጉዳት ስለመኖር አለመኖሩ በጥናቱ መካተቱንና ቦታውንም በመመልከት ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ሐ. አማካሪ ድርጅቱ የታደሰ የስራ ፍቃድ ማስረጃ ፎቶ ኮፒ በአባሪነት ማያያዙን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል::

መ. አማካሪ ድርጅቱ ተገቢውን የባለሙያዎች ስብጥር ያካተተ መሆኑን ማረጋገጥና ለዚህም የባለሙያዎቹ መረጃ/CV በአባሪነት መያያዙን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል:: በዚህም አማካሪ ድርጅቱና ተሳታፊ ባለሙያዎቹ የማማከር አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መያያዝ ይኖርበታል።

ሠ. የቀረበው ሰነድ በያንዳንዱ ገፅ ላይ በአማካሪ ድርጅቱ ማህተም የተረጋገጠ መሆኑን ማየት ይኖርባቸል::

፳ የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ሰነድ መያዝ ያለበት

ሀ. የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ሰነድ በቀላልና አሻሚ ባልሆነ ቋንቋ ተዘጋጅቶ ዝርዝር ቴክኒካዊ ትንታኔዎችንና መረጃዎችን ለምሳሌ ስለቦታው መገኛ፣ የመሬት አጠቃቀም፣ ካርታ፣ ፎቶ ግራፍ፣ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ሀብቶች ወዘተ… እንደአስፈላጊነቱ መያዝ ይኖርበታል።

ለ. የተፅዕኖ ግምገማ ለጥናቱ ዝግጅት የዋለ መረጃን፣ በጥናቱ ወቅት ያጋጠመ አጠራጣሪ ሁኔታን ወይም የዕውቀት ክፍተትን ማመልከት አለበት።

## ፲፪. የፕሮጀክቱ ባለቤት ግዴታዎች

ሀ. ማንኛውም የፕሮጀክት ባለቤት ፕሮጀክቱን ለማስጠናት ከባለሥልጣኑ ጋር ስላቀደው ፕሮጀክት መመካከር አለበት

ለ. ባለፕሮጀክቱ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሰነድ እንዲያስጠና ሲወሰን እንዲያሰራ በባለሥልጣኑ ከተለጠፈው ዝርዝር አማካሪ መርጦ ማሰራት ይጠበቅበታል።

ሐ. ማንኛውም የፕሮጀክት ባለቤት የፕሮጀክቱን የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አካሂዶ በቅድሚያ አሉታዊና አወንታዊ ተፅዕኖዎችን ለይቶ አሉታዊ ተፅዕኖዎች ቢቻል የሚወገዱበትን አለበለዚያ ደግሞ ተገቢውን የአካባቢ ደረጃዎች እንዲሟሉ የሚደረግበትን መንገድ በግልፅ ማስቀመጥ ይኖርበታል።

መ. የፕሮጀክቱ ባለቤት ለአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ሰነድ የሚያስፈልገውን ወጪ መሸፈን ይጠበቅበታል።

ሠ. የፕሮጀክቱ ባለቤት በአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ሰነድ ላይ የተዘረዘሩትን ግዴታዎች የማሟላት ግዴታ አለበት።

ረ. የፕሮጀክቱን ጥናት ስልጣን ካለው ከሚመለከተው አካል ሳይጸድቅ ወደሥራ መግባት የለበትም

ሰ. የፕሮጀክቱ ባለቤት ጥናት ሳያስጠና ወይም የተፈቀደለት የጥናት ሰነድ ጊዜው ካለፈ በኋላ እንደገና ሳያስጠና ፕሮጀክቱን መተግበር የለበትም

## ፲፫. የፀደቀ የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ሰነድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ የውሳኔ አሰጣጥ

ሀ. ተግባራዊ እንዲሆን ይሁንታ የተሰጠው ፕሮጀክት በጥናቱ ላይ በተመለከተው የጊዜና የሥራ መርሀ-ግብር መሰረት ተግባራዊ ካልሆነ ተፈፃሚነቱ ይቀራል፡፡

ለ. ነገር ግን በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 7.1 መሰረት ባለፕሮጀክቱ ተግባራዊ ያላደረገበትን አሳማኝና ተጨባጭ ምክንያት ካቀረበ በተለይም ጉዳዩ ከመንግስት ውሳኔ ሰጪ አካላት ጋር በተያያዘ መዘግየቱ የተፈጠረ ሆኖ ከተገኘ ባለሥልጣኑ ውሳኔውን ሊያጤን ይችላል፡፡

ሐ. የተለየ ሁኔታ ካላስገደደ በስተቀር በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 7.2 መሰረት ባለፕሮጀክቱ ያቀረበው አቤቱታ በ30 ቀናት ውስጥ የዘገባው ተቀባይነት ፀንቶ እንዲቆይ ወይም እንዲራዘም ወይም የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ሰነዱ እንዲከለስ ወይም እንደገና እንዲሰራ መወሰን አለበት፡፡

# ክፍል ሶስት

## ልዩልዩ ኃላፊነቶች

### ፲፬. ውሳኔ መስጠት (Decision Making)

ወሳኔ ለመስጠት በህግ ስልጣን የተሰጠው ለአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት ሲሆን በማዕከል ወይም በክፍለ ከተማ ውሳኔ የሚሰጠው በቀረበውን የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ሰነድ የመጀመሪያ ደረጃ ወይም ሙሉ ጥናት ሊሆን ይችላል፡፡ የአካባቢና ማህበረሰብ ግምገማ ሰነዶችን መርምሮ እና ፕሮጀክቱ ሊተገበር የታሰበበትን ቦታ ተመልክቶ፣ የአካባቢ ነዋሪዎችንና ለችግሩ ተጋላጭ የሆኑ የህበረተሰብ ክፍሎችንና ባለድርሻ አካላትን አማክሮ፣ የታሰበው ፕሮጀክት ያለውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታና የሚያስከትለውን አካባቢያዊ ጉዳት ከግምት ውስጥ በማስገባት ውሳኔው :-

፩ ፕሮጀክቱ የጎላ ችግር አያደርሰም ብሎ ካመነ ባለሥልጣኑ ስምምነቱን ወዲያውኑ ውሳኔውን ማወቅ ለሚገባው ወይም ለፈገው ወይም ለባለፕሮጀክቱ ወይም መንግስታዊ ወይም መንግስታዊ ላልሆነ አካል በፅሁፍ ያሳውቃል::

፪ በቀረበው ሰነድ ላይና ወይም በመስክ ምልከታ ወቅት የታዩትንና ወይም ሊከሰቱ ይችላሉ ተብለው የተገመቱትንና መስተካከል የሚገባቸውን ጉዳዮች እንዲስተካከሉ አስተያየት በመስጠትና መስተካከላቸውንም አረጋግጦ ባለሥልጣኑ ስምምነቱን/ውሳኔውን ማወቅ ለሚገባው ወይም ለፈገው ወይም ለባለፕሮጀክቱ ወይም መንግስታዊ ወይም መንግስታዊ ላልሆነ አካል ሊያሳውቅ ይችላል፡፡ የተለየ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር እጅግ ቢዘገይ በ15 የስራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

፫ በቀረበው ሰነድ ላይና ወይም በመስክ ምልከታ ወቅት እንደተገመተው የታሰበው ፕሮጀክት ሊያስከትል የሚችለው አካባቢያዊ ችግር የጎላ መሆኑ ከተገመተ ባለሥልጣኑ አሳማኝ የሆነ ምክንያቱን በማቅረብ የማይስማማ መሆኑን ውሳኔውን ማወቅ ለሚገባው ወይም ለፈገው ወይም ለባለፕሮጀክቱ ወይም መንግስታዊ ወይም መንግስታዊ ላልሆነ አካል ሊያሳውቅ

ይችላል፡፡ የተለየ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር እጅግ ቢዘገይ በ15 የስራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ያሳውቃል::

፬ ፕሮጀክቱ አነስተኛ ሆኖ የሚገመገመው በቼክሊስት ብቻ ከሆነ ፕሮጀክቱ የሚተገበርበትን ቦታ በመስክ በማየትና ለሥራ አመቺ መሆኑን በማጣራት ውሳኔውን ቢዘገይ በ3 የሥራ ቀናት ውስጥ በጽሑፍ ያሳውቃል።

፭ በፕሮጀክቱ ባህርይና መረጃ ችግር ምክንያት በክ/ከተማ ደረጃ ውሳኔ መስጠት ካስቸገረ በማዕከል ደረጃ እንዲታይ ሊወሰን ይችላል።

## ፲፭. ክዋኔ ኦዲት (ክትትልና ቁጥጥር) ማድረግ (Monitoring and Follow up)

በህግ ሥልጣን የተሰጠው የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት ማለትም በክፍለ ከተማ ወይም በማዕከል ደረጃ ሊሆን ይችላል።

፩ ቀደም ሲል በአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ያለፈ ፕሮጀክት በቀረበው ሰነድ መሰረት ወይም በተሰጠው መመሪያ መሰረት እየሰራ ስለመሆኑ ወይም ከአካባቢ ጋር በተጣጣመ መልኩ እየሰራ ስለመሆኑ ፕሮግራም ማስያዝ ወይም ቀድሞ ማሳወቅ ሳይጠበቅባችው የባለሥልጣኑ ተቆጣጣሪዎች መሆናቸውን የሚገልጽ መታወቂያ በማሳየት በማንኛወም ጊዜ ድንገተኛ ምልከታ ማድረግ፣ ፎቶግራፍ ማንሳት፣ ናሙና መውሰድ፣ ሰነዶችን ማገላበጥ፣ ድምፅ ወይም ሙቀት መለካት በአጠቃላይ ማንኛውንም መረጃ መጠየቅና ማግኘት ይችላሉ::

፪ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ያለበት ገና ፕሮጀክቱ ሲወጠን ጀምሮ ማንኛውም ፕሮጀክት ሊተገበር ሲታሰብ በፕሮጀክቱ ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ አወንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖዎችን በቅድሚያ መለየትና ማወቅ ስለሚገባ የሚመለከታቸውን ባለድረሻ አካላትን ማለትም ስለቦታው የመሬት አጠቃቀምና የወደፊት ዕድገት አቅጣጫ የአካባቢ ነዋሪዎች አስተያየት ለማግኘት ማነጋገርና ማማከር ይገባል

፫ ፕሮጀክቱ **በግንባታ** ላይ እያለ በአካባቢ ነዋሪዎች ላይ፣ በመሰረተ-ልማት አውታሮች ላይ፣ በአካባቢ ሥነ-ምህዳርና በመሳሰሉት ሊያስከትል ስለሚችለው አሉታዊ ተፅዕኖዎች የመቀነሻ ስልቶች በቀረበው ሰነድ ላይ በተገለፀው መሰረት ስለመተግበሩ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል።

ሀ. የተገባውን ግዴታ ተላልፎ ቢገኝም እንደሁኔታው በቃልም ሆነ በፅሁፍ ወይም በሁለቱም ማስጠንቀቂያ ከመስጠት አልፎ በየደረጃው እስከ ይሁንታ ማንሳት የሚደርስ እርምጃ ባለሥልጣኑ መውሰድ ይችላል።

ለ. ይሁንታው ሲነሳ ወይም የተሰጠው ፍቃድ ሲነሳ ወይም ሲሰረዝ ሌሎች ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች ውሳኔውን እንዲያውቁት በፅሁፍ ይገለፅላቸዋል። በዚህም መሰረት ቀደም ሲል የተሰጠውን ፍቃድ ማንሳት ወይም መሰረዝ ይጠበቅባቸዋል።

፬ ፕሮጀክቱ በትግበራ ላይ እያለ በተፅዕኖ ግምገማ ሰነዱ ላይ በተቀመጠውና ውል በገባው መሰረት ስለመተግበሩና አካባቢን ያገናዘበ ስለመሆኑ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ያስፈልጋል።

ሀ. የተገባውን ግዴታ ተላልፎ ቢገኝም እንደሁኔታው በቃልም ሆነ በፅሁፍ ወይም በሁለቱም ማስጠንቀቂያ ከመስጠት በየደረጃው እስከ ይሁንታ ማንሳት የሚደርስ እርምጃ ባለሥልጣኑ መውሰድ ይችላል።

ለ. ይሁንታው ሲነሳ ወይም የተሰጠው ፍቃድ ሲነሳ ወይም ሲሰረዝ ሌሎች ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች ውሳኔውን እንዲያውቁት በፅሁፍ ይገለፅላቸዋል። በዚህም መሰረት ቀደም ሲል የተሰጠውን ፍቃድ ማንሳት ወይም መሰረዝ ይጠበቅባቸዋል።

፭ ፕሮጀክቱ በሚዘጋበት ወይም ስራ በሚያቋርጥበት ወይም በሚያበቃበት ወቅት ፕሮጀክት ትቶት የሚሄደው አሻራ ማለትም እንደ የተረፈ ምርት ክምችት፣ ውጋጅ፣ የተፈጠሩ ጉድጓዶችና የተጎዱ መሬቶች፣ አገልግሎታቸውን ያቋረጡ ወይም የተበላሹ የስራ መሳሪያዎች ወዘተ… የመሳሰሉት በስርዓት ተወግደው ቦታው ቀድሞ ወደነበረበት ሁኔታ አገግሞ እንዲመለስ መደረግ ይኖርበታል።

## ፲፮. ነባር ተቋማት

በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሂደት ባለማለፋቸው በአካባቢ ላይ ሊያደርሱ የሚችሉትን ጉዳት ለመከታተል የሚያስችል ሰነድ ማዘጋጀት ይጠብቅባቸዋል።

፩ ነባር ተቋማት በአካባቢ ላይ እያደረሱ የነበረውን ጉዳት ለመከላከል የአካባቢ አያያዛቸውን ለመረዳትና ለመከታተል የሚያስችል የአካባቢ ማኔጅመንት(አያያዝ) እቅድ እንዲያቀርቡ ይደረጋል፣

፪ የአካባቢ አያያዝ ዕቅዱም በባለሥልጣኑ ባለሙያዎች በመስክም ጭምር ተገምግሞ የሚስተካከል ጉዳይ ካለ ታርሞ ይሁንታ ይሰጠዋል

፫ የሚያቀርቡት የአካባቢ አያያዝ እቅድ ሊከተሉ የሚችሉ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ለማስወገድ የሚያስችሉ እርምጃዎችን ማካተት አለበት

፬ በቀረበው የአካባቢ አያያዝ ዕቅድ መሠረት ያልፈፀሙ ተቋማት ላይ ክትትል በማድረግ እርምጃ ይወሰዳል።

፭ በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሂደት ያላለፈ ተቋም የሚገኝበትን ሁኔታ ለመረዳት የአካባቢ ኦዲት ግኝቱን ሪፖርት ማዘጋጀትና ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት

፮ ድርጅቱ የሚቀርበው የኦዲት ሪፖረት በባለሥልጣኑ ባለሙያዎች ተገምግሞ ግብረመልስ ይሰጠዋል፤ የኦዲት ግኙቱ በአካባቢ ላይ እየደረሰ ያለ አሉታዊ ተፅዕኖ መሆኑን ካመላከተ የኦዲት ግኙቱን ለማረም የአካባቢ አያያዝ ዕቅድ እንዲያቀርብ ሊጠየቅ ይችላል።

፯ ነባር የኢንዱስትሪ ተቋማት በማምረት ሂደት የሚያስከትሉትን ብክለት ለመከላከልና የጥሬ ዕቃ፣ የውሃና ኢነርጂን ጨምሮ የሀብት ብክነት እንዲቀነሱ የንጹህ ማምረት ዘዴን (Cleaner Production) እንዲተገብሩ ይደረጋል።

## ፲፯. የአዲስ ሁኔታ መከሰት

የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ሰነድ ዘገባ በቀረበበት ወቅት ያልተጤነ አካባያዊ ችግር በትግበራ ወቅት ተከስቶ ቢገኝ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሰነዱ እንዲከለስ ወይም እንደገና እንዲዘጋጅ ማድርግ ይችላል፡፡

## ፲፰. በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ላይ ሊደረግ ስለሚገባ የህብረተ-ሰብ ተሳትፎ

በማንኛውም የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘገባ ወቅት የአካባቢው ህብረተሰብ አስተያየት መጠየቅ ይኖርበታል፡፡ በቀረበው የጥናት ሰነድ ላይ የህብረተሰቡ አስተያየት በአባሪነት መያያዝ ይኖርበታል፡፡ አጠራጣሪ ሁኔታ ተከስቶ ቢገኝ የባለሥልጣኑ ባለሙያዎች የችግሩ ተጠቂዎች ናቸው ተብለው የሚገመቱ የህብረተሰብ ክፍሎችን በመስክ ምልከታ ወቅት አስተያየታቸውን መቀበል ይጠበቅባቸዋል፡፡

## ፲፱. ስለማበረታቻ

አካባቢን ያገናዘበና ሰላማዊ የአመራረት ዘዴን ተከትለው የሚያመርቱ ፕሮጀክቶችን ባለሥልጣኑ ለማበረታታት ዕውቅና (ሰርተፊኬት) ይሰጣል፣ ያበረታታል፣ ለዚሁ ዓላማ የሚውሉ የስራ መሳሪያዎች ከቀረጥ ነፃ የሚገቡበትን ሁኔታዎች ለማመቻቸት ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት የትብብር ድጋፍ ይፅፋል፡፡

## ፳. የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት

፩ ለፕሮጀክት ትግበራ በተሰጠ ይሁንታ ወይም በክትትል ወይም ፕሮጀክቱን በሚመለከት በባለሥልጣኑ በተሰጠ በማንኛውም ሌላ ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ቅሬታውን ለባለሥልጣኑ ሥራአስኪያጅ ማቅረብ ይችላል፡፡

፪ የፕሮጀክት ጥናቱ ውድቅ የተደረገበት የፕሮጀክት ባለቤት ቅሬታውን በ10 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይችላል፡፡

፫ በዚህ አንቀፅ ንዑሥ አንቀፅ 1 በተደነገገው መሰረት የቀረበውን ቅሬታ የባለሥልጣኑ ሥራአስኪያጅ ወይም ኃላፊ ወይም መሪ ቅሬታውን አጣርቶ በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ በጽሑፍ ይሰጣል፡፡

፬ የባለሥልጣኑ ሥራአስኪያጅ ወይም ኃላፊ ወይም መሪ ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል ፡፡ ነገር ግን በውሳኔው ቅር የተሰኘ ወገን ጉዳዩን ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት እንዲታይለት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

## ፳፩. የተከለከሉ ተግባራት

፩ የፕሮጀክት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሳያስጠና ስራ መጀመር የተከለከለ ነው፡፡

፪ በፕሮጀክት ጥናቱ ከተመለከተው ውጭ በቦታው ላይ ሌላ ሥራ መስራት ክልክል ነው፡፡

፫ የፕሮጀክት ጥናቱ ጸድቆ እንዲተገበር የታቀደለት ጊዜ ካለፈ በኋላ ሳያሳውቁ መስራት ክልክል ነው፡፡

፬ ይሁንታ ከተሰጠው የፕሮጀክት ሰነድ ውጭ ሲሰሩ መገኘት እና ስምምነቶችና ግዴታውችን መጣስ ክልክል ነው፡፡

፭ ፕሮጀክቱ አካባቢን በሚጎዳ መልኩ መተግበርና መምራት ክልክል ነው፡፡

**፳፪. ተጠያቂነት**

ማንኛውም ሰው ወይም የፕሮጀክት ባለቤት አዋጅና ደንቦች የተቀመጡ ድንጋጌዎችን ወይም ይህን መመሪያ በመተላለፍ ፕሮጀክቱ ለሚያስከትለው ጉዳት ወይም ከፕሮጀክቱ ጥናት ውጭ ከፈጸሙ በየትኛውም መልኩ የተከለከሉ ተግባራትን የፈጸሙ እንደሆነ አግባብ ባላቸው ህጎች መሠረት ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

**፳፫. ጥቆማን የማቅረብ መብት**

የፕሮጀክቱ መካሄድ በሰውና በሕይወት ላይ ጉዳት የሚያስከትል ከሆነ ማንኛውም ሰው ጥቆማ የማቅረብ መብት አለው፡፡

# ክፍል አራት

## የኃላፊነት ወሰን

**፳፬. የሥራ ክፍፍል**

፩ ባለሥልጣኑ በማዕከልና በክፍለ-ከተማ ደረጃ የሚታዩትንም ፕሮጀክቶች በይዘታቸውና መጠናቸው ለይቶ ባለጉዳዮች በዚያው ደረጃ በሚገኙ የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች እንዲስተናገዱ ያደርጋል፡፡ እንደሥራው ባህርይና አደረጃጀት ሁኔታ ፕሮጀክቶች የሚታዩበትን ቦታ ሊቀይር ይችላል፡፡

፪ በማዕከል ደረጃ የሚታዩ ፕሮጀክቶች ሙሉ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሰነድ የሚቀርብባቸው ሲሆኑ በክፍለ-ከተማ ደረጃ የሚታዮ ፕሮጀክቶች እንደባህሪያቸው ከፊል የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሰነድ የሚቀርብባቸው ወይም በቼክሊስት የሚገመገሙ ይሆናሉ፡፡

፫ በማዕከል ፕሮጀክቶች የሚገመገሙት በፌደራል የአካባቢ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ደረጃ በተዘጋጀው ጋይድላይን መሠረት ሲሆን በማዕከል የፕሮጀክቶችን አተገባበር፣ አካባቢ አያያዝ እቅድ ወይም ኦዲት ግኝት ክትትል ማድረጊያ ቼክሊስት፣ ክፍለ-ከተሞች የሚጠቀሙበት ቼክሊስትና በግምገማ ወቅት ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች (አመላካቾች) ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዘዋል

፬ በየደረጃው የተለዩት ፕሮጀክቶች ዝርዝርም የሚከተለውን ይሆናል፤ ፕሮክቶቹም በዝርዝሩ መሠረት በየደረጃው የሚገመገሙ ይሆናል

**፳፭. በማዕከል የሚገመገሙ ፕሮጀክቶች ዝርዝር**

፩ የምግብና መጠጥ ኢንዱስትሪዎች

ሀ. የእንስሳትና ዕፅዋት ተዋጽኦ ዘይት ማምረት
ለ. የሥጋ ውጤቶች ማምረት
ሐ. የቢራ ማምረት
መ. የዓሣ ተዋጽኦ ማምረት
ሰ. ቄራዎች
ረ. ለስላሳ መጠጥ ማምረት
ሸ. ትንባሆ ማምረት
ቀ. ስኳር ማምረት
በ. ሌሎች የአግሮ ፕሮሰስ ማምረቻ

፪ የጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ

ሀ. ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ

ለ. የጥጥና ሲንቴቲክ ፋይበር ማምረት

ሐ. ጥጥን ከፍሬ የመለየት / ginneries/

መ. የልብስ ስፌት - ከ50 የስፌት ማሽን በላይ

፫ የቆዳ ኢንዱስትሪ

ሀ. ቆዳ ፋብሪካ

ለ. ቆዳ ማልፋት

ሐ. የቆዳ ማጠናቀቅ

መ. የቆዳ ውጤቶች /ጫማ፣ ልብስ/ ፋብሪካ

ሠ. የቆዳ መጋዘን ከ500 ካሬ በላይ

፬ የእንጨት፣ ፐልፕና ወረቀት ኢንዱስትሪ

ሀ. ቺፕውድ፣ ኮምፐርሳቶ፣ ቦርድ

ለ. ፐልፕ፣ ወረቀት፣

፭ የግንባታ ዘርፍ

ሀ. የሪልስቴትና ኢንዱስትሪ ፓርኮች

ለ. ገበያ ቦታዎች፣ የተሽከርካሪ ማቆሚያዎች-እንደ ከተማ ለሚዘጋጁ

ሐ. ህንፃዎች፣ ከ7 ወለል በላይ

መ. ሆስፒታሎች፣

ሠ. ት/ቤቶች- ከሁለተኛ ደረጃና በላይ

ረ. ሆቴሎች፣ ኮከብ 3 እና ከዚያ በላይ

ሰ. የመንገድ፣ ኤርፖርት፣ ባቡር መንገድ፣ ቧንቧ መስመር፣ ወዘተ መገንባትና ማስፋፋት

ሸ. የወንዝ ማፋሰሻና ጎርፍ መከላከል ሥራዎች

ቀ. የሃይድሮኤሌክትሪክና የመስኖ ግድቦች

በ. የእንስሳት እርባታ/ማደለብ - የቀንድ ከብት ከ100 በላይ፣ ዶሮ ከ5000 በላይ

፮ ኬሚካል ኢንዱስትሪዎች

ሀ. አደገኛና መርዛማ ኬሚካሎችን ማምረት፣ ማጓጓዝ፣ ማከማቸትና መጠቀም

ለ. የመድሃኒት ማምረቻ

ሐ. የነዳጅ፣ የፔትሪኬሚካልና ሌሎች የኬሚካል ምርቶች ማከማቻ (ማደያዎች)

መ. የነዳጅ ማጣሪያ፣ የነዳጅ ምርቶች ፕሮሰስ ማድረግና ማጓጓዝ

ሠ. የቀለም፣ ቫርኒሽ፣ ወዘተ ማምረት

፯ የማዕድን ማውጣት

ሀ. የኮንስትራክሽን ማዕድን ማምረት

ለ. ሌሎች ሚነራሎችን ማውጣት፣ ፕሮሰስ ማድረግ

፰ ብረት ነክ ያልሆኑ ኢንዱስትሪዎች

ሀ. ሲሚንቶ፣ አስቤስቶስ፣ መስታወት፣ ወዘተ ማምረት

ለ. የጎማ ማምረት
ሐ. ስፖንጅ ፋብሪካ
መ. የፕላስቲክ ማምረት - 100 ካሬሜትር ቦታ በላይ

፱ ብረታብረትና ኢንጂነሪንግ
ሀ. ተሽከርካሪና ሌሎች መጓጓዣዎችን ማምረት፣ መገጣጠም
ለ. የተለያዩ አካላትን ማምረት /body - building/
ሐ. ቦይለር፣ ማጠራቀሚያ ታንከሮችን መስራት
መ. ማቅለጫና ቅርጽ ማውጫ
ሠ. የተለያዩ ቁሳቁሶችን ማምረት
ረ. ለሌሎች ማምረቻዎች የሚያገለግሉ ብረታብረቶችን ማምረት
ሰ. ኤሌክትሮፕሌቲንግ

፲ የቆሻሻ ማጣራትና ማስወገድ
ሀ. የአደገኛ ቆሻሻዎች ማቃጠያ፣ መልሶ መጠቀሚያ፣ ማከማቻ፣ መቅበሪያ፣ ማጣሪያ፣ መሰባሰብና ማጓጓዝ፣ ማስወገድ
ለ. የማዘጋጃ ደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብና ማጓጓዝ፣ ማከማቻ፣ መልሶ መጠቀሚያ ፕላንት፣ ማቅለዣ ፕላንት፣ ማስወጋጃ ቦታ
ሐ. የከተማ ፍሳሽ ማጣሪያ፣ የፍሳሽ መስመር ዝርጋታ፣ የተመጠጠ ፍሳሽ ማጓጓዝና ማጣራት

፲፩ የውሃ አቅርቦት
ሀ. የውሃ ማጣራት፣ ከጉድጓድ ማውጣት፣ ግድብና ማጠራቀሚያ መስራት
ለ. ውሃን በብዛት አውጥቶ ለኢንዱስትሪ፣ ለመስኖ፣ ወዘተ መጠቀም
ሐ. ውሃን በተዘጋጀ ካናል ማስኬድ፣ የተፈጥሮ አቅጣጫን ማስቀየር

፲፪ ግብርና/ተፈጥሮ ሃብት ዘርፍ
ሀ. የመስኖ ውሃ አጠቃቀም
ለ. የአዳዲስ ዝርያ፣ ማዳበሪያና ኬሚካል አጠቃቀም
ሐ. የደን ውጤቶችን ማምረት
መ. የደን ማልማት፣ የደን መቁረጥ፣ የደን መሬት አጠቃቀም መቀየር
ሠ. በተራራማ ቦታዎች ላይ መዝናኛ ሪዞርት/ሆቴል መስራት፣ በደን ክልል ውስጥ የቱሪስት መዝናኛ መስራት
ረ. ሰው-ሰራሽ የዓሳ ማራቢያ ቦታ ማዘጋጀት
ሰ. የዱር እንስሳት ማራቢያ ቦታ ማዘጋጀት

፲፫ ኢነርጂ ዘርፍ
ሀ. ኤሌክትሪክ አመንጪቶ ማሰራጨት
ለ. ከፍተኛ ማሰራጫ መስመሮችና ስቴሽኖች
ሐ. የሃይድሮ፣ የነፋስ፣ የባዮማስ፣ የጸሃይ፣ የእንፋሎት ሃይል ማመንጫዎች

፲፬ የተጎዱ ቦታዎችን ማስተካከል፣ የተበከለ አካባቢን ማጽዳት

፲፭ የተፈናቀሉ ማህበረሰብን ማስፈር

## ፳፮. <u>በክፍለ-ከተማ ደረጃ የሚገመገሙ ፕሮጀክቶች ዝርዝር</u>

፩ አነስተኛ የምግብ ዘይት መጭመቂያ
፪ ጋራዥ፣ ከጋራዥ ጋር ተያይዥነት ያላቸው የቦዲና ቀለም ቅብ ስራዎችና የመኪና እጥበት
፫ መለስተኛ የጤና ተቋማት/ ጤና ጣቢያ፣ መለስተኛና መካከለኛ ክሊኒክ/
፬ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች /የእንጨት፣ ቀርከሃ፣ የብረታ ብረትና የመስታወት/ ስራዎች
፭ የብሎኬት ፣ የጡብ/ ሸክላ ማምረቻዎች
፮ የድርና ማግ ማንጣትና ማቅለም
፯ አነስተኛ ሆቴሎች - ከ2 ኮከብ ያልበለጠ
፰ አነስተኛ የእንስሳት እርባታ/ማደለብ
ሀ. የቀንድ ከብት - ከ100 የማይበልጥ
ለ. ዶሮ - ከ5000 የማይበልጥ
፱ አነስተኛ የልብስ ስፌት ፋብሪካ
፲. አነስተኛ ህንጻ ግንባታ - እስከ 7 ወለል ላሉት
፲፩. የኮብልስቶን መንገዶችና ድሬኔጅ
፲፪. አነስተኛ ፕላስቲክ ፋብሪካ- እስከ 100 ካሬሜትር ቦታ ላይ ለሚሰራ
፲፫. መጋዘን ከ100 ካሬ ሜትር በላይ
ሀ. የቆዳ መጋዘን ከ500 ካሬ ሜትር በታች
፲፬. የእህል ማበጠሪያ
፲፭. የፍራፍሬ ጭማቂዎች ማምረት
፲፮. የኖራ፣ ታይልስ፣ ሴራሚክ፣ እብነበረድ፣ ወዘተ ማምረት
፲፯. ገበያ ቦታዎች፣ የተሽከርካሪ ማቆሚያዎች- በክ/ከተማ ደረጃ
፲፰. የወተት ተዋጽኦ ማምረት
፲፱. የጨርቅ ማቅለም
፳. ት/ቤቶች - ከሁለተኛ ደረጃ በታች
፳፩. የኤሌክትሪክና መገዶ ቆጣቢ ምድጃ ማምረት
፳፪. የሴፍቲኔት ፕሮጀክቶች
፳፫. የምሽት ክበቦች (ባር፣ ሬስቶራንት፣ ግሮሰሪ)
፳፬. የሻማ ማምረት ሥራ
፳፭. አሸንዳና ቦሮንዳዮ ማምረት
፳፮. የታፕሴሪ ሥራ
፳፯. የስፖንጅ ውጤቶች ማምረት (ቁርጥራጭ ተጠቅሞ)
፳፰. የወርቅና ጌጣጌጥ ሥራዎች
፳፱. ጠላት የቀበረው ንብረት ማውጣት
፴. የወፍጮ ቤት (እህል፣ በርበሬ፣ ቅመማቅመም)

፴፩.የፎቶ ስቱዲዮ ማቋቋም

፴፪. የሙዚቃ ስቱዲዮ፣ ዲኤስ ቲቪና ቪዲዮ ቤት

፴፫. ዳቦና ኬክ መጋገሪያ ቤቶች

፴፬. የልብስ እጥበት /በእጅና በላውንደሪ/

፴፭. አነስተኛ የምግብ ማቀነባበሪያና ማሽጊያ፣

ሀ. ቆሎ ማዘጋጀት፣ ገብስ መፈተግ፣

ለ. እንጀራ መጋገር፣

ሐ. ሽንኩርት መፍጨት፣ ወዘተ

፴፮.የብረታብረት ውጤቶችን በእጅ ማምረት

፴፯.ሻወር ቤት

፴፱.አነስተኛ ባህላዊ መጠጥ ቤቶች

ከተ.ቁ ፩-፳ ላሉት ፕሮጀክቶች ከፊል የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ሰነድ መቅረብ ያለበት ሲሆን፣ ከተ.ቁ. ፳፩-፴፱ በቼክሊስት የሚስተናገዱ ይሆናል።

# ክፍል አምስት

## ስለ ጥፋትና ቅጣት

### ፳፱. <u>ልዩልዩ አስተዳደራዊና የቅጣት እርምጃዎች</u>

፩ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ መሰረት የማይካሄድ ፕሮጀክት ጉዳት እያደረሰ ከሆነ የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ሳያስጠና የሚሰራ ፕሮጀክት ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ አፋጣኝ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡

፪ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ የተሰጠው አካል የሚሰራውን ፕሮጀክት በማቆም በደረሰው ማስጠንቀቂያ መሰረት በባለሥልጣኑ መ/ቤትና በክ/ከተማ ጽ/ቤቶች ወዲያውኑ ሪፖርት በማቅረብ በሚሰጡት ውሳኔ መሰረት በቀጣይ ጊዜያት በአካል ቀርቦ በጽሑፍ ምላሽ መስጠት አለበት፡፡ ያቀረበው አስተያየት አሳማኝ ከሆነ እና ለመዘገየቱ መረጃ ካቀረበ በባለሥልጣኑ ወይም በክ/ከተማ ጽ/ቤቶች ተጨማሪ ጊዜ ሊሰጠው ይችላል፡፡

፫ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ የተሰጠው ድርጅት ወይም የፕሮጀክት ባለቤት ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው ጊዜ ጀምሮ የሚደርሰውን ጉዳት ካላስተካከለ ባለሥልጣኑ፣ የክ/ከተማ ጽ/ቤቶች ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ አስተዳደራዊ የቅጣት እርምጃ ይወስዳል፡፡

፬ ማንኛውም የፕሮጀክት ባለቤት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ እንዲያካሂድበት የተደነገገበትን ማንኛውንም ፕሮጀክት ከባለሥልጣኑ ይሁንታ ሳያገኝ ተግባራዊ ያደረገ እንደሆነ ወይም በአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባ ውስጥ ሀሰተኛ ዘገባ ያቀረበ እንደሆነ፤ ወይም ከተፈደለት ሥራ ውጭ ሰርቶ ከተገኘ ወይም በሥራው ምክንያት አካባቢ ላይ ጉዳት ካደረሰ ከ50 ሺ.ህ ብር በማያንስና ከ100 ሺ.ህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል፡፡ ማንኛውም የኦዲት ሪፖርት ወይም የአካባቢ አያያዝ ዕቅድ እንዲያቀርብ ሲገባው ያላቀረበ ሰው፣ ባቀረበው ሪፖርት መሠረት ያልተገበረ ሰው ጥፋት ፈፅሟልና በ10 የስራቀናት ውስጥ እንዲያስተካክል የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡ በህግ

የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ጥፋት ፈጽሞ ሲገኝ የህጉን መከበር ለማረጋገጥ መፈፀም የሚገባን ተግባር በትጋት ያልተወጣ በመሆኑ የድርጅቱ የሥራ መሪ በንዑስ አንቀፅ ፬ ከዚህ በላይ በድርጅቱ ላይ ከተጣለው ቅጣት በተጨማሪ ከ5 ሺህ ብር በማያንስና ከ10 ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል፡፡ ለተፈፃሚነቱም በህግ ሥልጣን የተሰጠው የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ጉዳዩን ለህግ በማቅረብ ተግባራዊ እንዲሆን ክትትል ያደርጋል፡፡

ሀ. ፕሮጀክቱ አካባቢን በሚጎዳ መልኩ መተግበርና መምራት በዚህም በሰውና ንብረት ላይ ጉዳት ከደረሰ ለደረሰው ጉዳት ካሳና የ100,000 ብር ያስቀጣል፡፡

ለ. የፕሮጀክት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሳያስጠና ስራ መጀመር 90,000 ብር ያስቀጣል

ሐ. በፕሮጀክት ጥናቱ ከተመለከተው ውጭ በቦታው ላይ ሌላ ሥራ መስራት 80,000 ብር ያስቀጣል፡፡

መ. የፕሮጀክት ጥናቱ ጸድቆ እንዲተገበር የታቀደለት ጊዜ ካለፈ በኋላ ሳያሳውቁ መስራት 50,000 ብር ያስቀጣል፡፡

ሠ. ማንኛውም የኦዲት ሪፖርት ወይም የአካባቢ አያያዝ ዕቅድ እንዲያቀርብ ሲገባው ያላቀረበ ሰው፣ ባቀረበው ሪፖርት መሠረት ያልተገበረ ሰው ጥፋት ፈፅሟልና በ10 የስራቀናት ውስጥ እንዲያስተካክል የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡ በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ካላስተካከለ 50 ሺህ ብር የገንዘብ መዋጮ ይቀጣል

ቀ. ድርጅቱ መፈጸም ያለበትን የሥራ ተግባር ያልፈጸመ የድርጅቱ መሪ የህጉን መከበር ለማረጋገጥ መፈፀም የሚገባን ተግባር በትጋት ያልተወጣ ከሆነ ከዚህ በላይ በድርጅቱ ላይ ከተጣለው ቅጣት በተጨማሪ የድርጅቱ መሪ 10 ሺህ ብር የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል፡፡

፫ የመጀመሪያ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት እና የገንዘብ ቅጣት ተቀጥቶ ያላስተካከለ ከሆነና በድጋሚ ጥፋት ከፈፀመ ለፈፀመው ጥፋት የፕሮጀክቱን ባለቤት ተጠያቂ በማድረግ ተቋሙ እንዲዘጋ ይደረጋል፡፡

፬ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲያቆም የተደረገ ድርጅት ወይም ተቋም የፕሮጀክቱ ባለቤት ለፈጸመው ጥፋት በቂ ምክንያት ከማስረጃ ጋር ካቀረበ ባለሥልጣኑ የቀረበውን ማስረጃ አሳማኝ ሆኖ ካገኘው ባለሥልጣኑ በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት ስራውን እንዲቀጥል ማድረግ ይችላል፡፡

፭ በደንብ ተላላፊዎች ላይ የወንጀለኛ መቅጫ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ መሰረት የወጣውን ደንብ ተላልፎ የተገኘ ሰው በወንጀልም በፍትሃብሄርም ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፰ ይህንን መመሪያ በመጣስ ጥፋተኝነቱ የተረጋገጠበት ሰው ከሚወሰንበት ከማንኛውም ቅጣት በተጨማሪ የደረሰውንና ወደፊት ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት በሙሉ በራሱ ወጪ እንዲያስተካክል ወይም እንዲተካ ይደረጋል፡፡

## ፳፱. ጥፋት ፈጸሞ የተገኘ ባለሙያ

፩ የባለሥልጣኑ ባለሙያ ሆኖ ከባለፕሮጀክቱ ባለቤትም ሆነ ከአማካሪው ጋር በመገናኘትና በመመሳጠር ያለአግባብ መረጃ በማውጣት ሲሰራ የተገኘ ለፈጸመው የሥነምግባር ግድፈት የመጀመሪያ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡

፪ በባለሥልጣኑ የተገመገሙ የአካባቢ ተፀዕኖ ግምገማ ሰነዶች መረጃ ያለኮሚሽኑ ፈቃድ በማውጣት ለማይመለከተው አካል አሳልፎ መረጃ ከሰጠ በከባድ የሰራተኛ አስተዳደርና የዲሲፕሊን ህግ መሠረት የ 1ወር ደሞዝ ይቀጣል፡፡

፫ የባለሥልጣኑ ባለሙያ የመጀመሪያ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ደርሶት ካላስተካከለና በድጋሚ ጥፋት ሲፈጽም ከተገኘ የደሞዝ ቅጣትና ከሥራ ሊታገድ ይችላል፡፡

## ፴፩. ስለፍታብሔር ኃላፊነት

፩ ማንኛውም ሰው ወይም የፕሮጀክት ባለቤት ይህን መመሪያ በመተላለፍ ወይም በመጣስ በአካባቢው ላይ ለሚደርሰው ጉዳት በሰዎች ደህንነት አኗኗር እና ቁሳዊ ጥቅሞች ላይ ለሚደርሰው ጉዳት እንደ ጉዳቱ አይነትና መጠን፡-

ሀ. ያደረሰውን ጉዳት ወደነበረበት ሁኔታ በራሱ ወጭ መልሶ የማስተካከል ግዴታ አለበት፡፡

ለ. በሰዎች ህይወት እና ንብረት ላይ ያደረሰውን ጉዳትና መጠን በህጉ ላይ በተቀመጠው መሰረት የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

፪ ማንኛውም ፕሮጀክት የአካባቢና ማህበረሰብ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት መሰረት ፕሮጀክቱን የመፈጸም ኃላፊነት ያለበት ሲሆን ከዚህ ጋር በተገናኘ ፕሮጀክቱ ጉዳት ሲያደርስ ጉዳቱ የቀረበለት የፍትህ ተቋም ፕሮጀክቱ ያደረሰውን ጉዳት ያስከተለው ውጤት መሰረት አድርጎ የጉዳት ካሳ እንዲከፍል በሚቀርበው ማስረጃ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ፴፪. ስለወንጀል ኃላፊነት

፩ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ መሰረት የደረሱ ጥፋቶችን ለማረም የሚወሰድ እርምጃ

ሀ.የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎችን የተላለፈ ማንኛውም ሰው ወይም የፕሮጀክት ባለቤት ወይም ድርጅት በመመሪያው በተላለፈው ዝርዝር መሰረት በሰራው ጥፋት እርምጃ ይወሰዳል፡፡

ለ. ፕሮጀክቱ ለደረሰው ጥፋት አይት  በቀጣይ አደገኛ ጉዳት ያደርሳል ተብሎ በሚታሰብ ጊዜ ማስጠንቀቂያ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላስተካከለ ወይም ካልፈፀመ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለሚመለከተው ፍትህ አካላት በማሳወቅ ድርጅቱ እንዲዘጋ ወይም ስራውን እንዲያቆም ያደርጋል፡፡

## ክፍል ስድስት
## ልዩልዩ ድንጋጌዎች

**፴፫. <u>የመፈፀም ግዴታ</u>**

ለዚህ መመሪያ አተገባበር ማንኛውም ሰው የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**፴፬. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>**

ይህ መመሪያ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**፴፭. <u>መመሪያውን ስለማሻሻልና ስለሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ መመሪያ እንደአስፈላጊነቱ ከወቅቱ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ሊሻሻል ይችላል፡፡

**፴፮. <u>ይህ መመሪያ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

የአፈጻጸም መመሪያው በልዩ ሁኔታ በባለሥልጣኑ መ/ቤት ታይቶ ከጸደቀበት ከ----/2014 ጀምሮ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ሲሳይ ጌታቸው አበራ

---/2014 ዓ.ም.

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ሥራአስኪጅ

# አባሪ 1

## በክ/ከተማ ሁሉንም ቦታዎች ለመገምገም የሚያገለግል ቼክሊስት

1. የፕሮጀክቱ ባለቤት ስም………………ክ/ከተማ……….ወረዳ………ስልክ ቁጥር……
2. የፕሮጀክቱ ስም-----------------------------------------------------------------------------------
3. የፕሮጀክቱ የስራ ዓይነት /ባህሪ/…………………………………………………..
4. ፕሮጀክቱ የሚገኝበት አድራሻ፤ ክ/ከተማ………………… ወረዳ ……………
5. ፕሮጀክቱ ጂኦግራፊያዊ ኮኦርዲኔት፤ X፡---------------------Y፡---------------Alt.---------

| ተ.ቁ | በቀረበው የፕሮጀክት ሃሳብና መስክ ምልከታ የሚታየው ጉዳይ | አዎን | አይደለም | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ፕሮጀክቱ የሚገነባበት ቦታ ለዚህ ሥራ (ከመሬት አጠቃቀም አንጻር) የተፈቀደ ነው? | | | |
| 2 | ፕሮጀክቱ የሚገነባበት ቦታ ካርታ ወይም የኪራይ ውል አለው? | | | |
| 3 | ስለፕሮጀክቱ ምንነትና አተገባበር አዋሳኞች/አጎራባቾች ያውቃሉ? | | | |
| 4 | ፕሮጀክቱን የሚያዋስኑት አጎራባቾች በፕሮጀክቱ ላይ ተቃውሞ አላቸው? | | | |
| 5 | የፕሮጀክቱ አዋሳኝ ማህበረሰብ ፕሮጀክቱ ጠቀሜታ እንዳለው ያምናል? | | | |
| 6 | የፕሮጀክቱ ሥራ ከመኖሪያ ቤት ያለው ርቀት በቂ ነው? (ርቀቱ እንደፕሮጀክቱ ባህርይ የሚለያይ ሆኖ ሽታ፣ ብናኝ፣ ንዝረት፣ ድምጽ ካለው ከ50 ሜትር ባያንስ) | | | |
| 7 | ፕሮጀክቱ የሚተገበርበት ቦታ ላይ ለፕሮጀክቱ ዋንኛ ሥራ ተብሎ የሚገነባው ወለል/ግድግዳ የተሰራው በቀላሉ ከማይፈርስ ማቴሪያል ነው? | | | |
| 8 | በፕሮጀክቱ ምክንያት የሚፈናቀል የህብረተሰብ ክፍል አለ? ካለስ ካሳ ተከፍሎታል? | | | |
| 9 | በፕሮጀክቱ ግንባታ ምክንያት የሚወገድ/የሚጎዳ የተፈጥሮ ሃብት ወይም ባህላዊ/ታሪካዊ ቅርስ አለ? | | | |
| 10 | ፕሮጀክቱ **በግንባታ ወቅት** የሚፈጥረው ድምጽ ወይም ብናኝ ወይም በግንባታ ዕቃዎች አቀማመጥ መንገድ መዘጋት/ማበላሸት ወይም የከባድ ተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ ሁከት ወይም በሚወገድ ቆሻሻ/ፍሳሽ/ጎርፍ ምክንያት በአካባቢው ነዋሪዎች ላይ የሚያስከትለው ችግር ይኖራል? | | | |
| 11 | ፕሮጀክቱ **በግንባታ ወቅት** የሚደርሰውን ችግር ለማቃለል ባለፕሮጀክቱ ያስቀመጠው መፍትሄ አለ? | | | |
| 12 | ፕሮጀክቱ ወደ **ተግባር/ማምረት ሲገባ** ደረቅ ቆሻሻን ያመነጫል? | | | |
| 13 | ፕሮጀክቱ ወደ **ተግባር/ማምረት ሲገባ** ደረቅ ቆሻሻን የሚያመነጭ ከሆነ አካባቢን ሳይበክልና ማህበረሰቡን ሳይጎዳ ባግባቡ ይወገዳል? | | | |
| 14 | ፕሮጀክቱ ወደ **ተግባር/ማምረት ሲገባ** ፍሳሽ ቆሻሻን ያመነጫል? | | | |
| 15 | በፕሮጀክቱ የሚመነጨው ፍሳሽ ወደ አካባቢው ወንዝ ወይም ድሬኔጅ ይለቀቃል? | | | |

| ተ.ቁ | በቀረበው የፕሮጀክት ሃሳብና መስክ ምልከታ የሚታየው ጉዳይ | አዎን | አይደለም | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|---|
| 16 | ፕሮጀክቱ ወደ ተግባር/ማምረት ሲገባ ፍሳሽ ቆሻሻን የሚያመነጭ ከሆነ አካባቢንና ማህበረሰቡን በማይበክል ሁኔታ ባግባቡ ይወገዳል? | | | |
| 17 | ፕሮጀክቱ ወደ ተግባር/ማምረት ሲገባ ጭስ፣ ሽታ፣ ብናኝ ያመነጫል? | | | |
| 18 | ፕሮጀክቱ ወደ ተግባር/ማምረት ሲገባ ጭስ፣ ሽታ፣ ብናኝ የሚያመነጭ ከሆነ የመቀነስ/የማስወገድ ዘዴ ይጠቀማል? | | | |
| 19 | ፕሮጀክቱ ወደ ተግባር/ማምረት ሲገባ በማሽኖች እንቅስቃሴ ወይም ሌላ ምክንያት ድምጽ ይፈጠራል? | | | |
| 20 | በማምረት ሂደት የሚፈጠር ድምጽ በአዋሳኝ የሚገኙ ነዋሪዎችን ሊያውክ ይችላል? | | | |
| 21 | በማምረት ሂደት የሚፈጠር ድምጽን ለመቀነስ/ለማስወገድ የታቀደ ሥራ አለ? | | | |
| 22 | በፕሮጀክቱ የሚገነባው ህንጻ/መጋዘን/ፋብሪካ በቂ የአየር ዝውውር እንዲኖረው ተደርጎ ነው? | | | |
| 23 | ለሠራተኛ ደህንነት የሥራ ልብስ ማለትም -እንደአስፈላጊነቱ የሥራ ልብስ፣ ጫማ፣ የአፍና አፍጫ መሸፈኛ፣ የጆሮ መከላከያ ይሰጣል? | | | |
| 24 | ፕሮጀክቱ ለሠራተኞቹ ስለሥራ ላይ ደህንነትና አካባቢ ጥበቃ ስልጠና ይሰጣል? | | | |
| 25 | ፕሮጀክቱ ለሚደርሱ ድንገተኛ አደጋዎች (የእሳት፣ የፍንዳታ፣ የጎጂ ነገሮች ማፈትለክ፣ ወ.ዘ.ተ) ቅደመዝግጅት አድረጓል? ለዚህ አመላካች ምልክቶች ይኖራሉ? | | | |
| 26 | የፕሮጀክቱ ዲዛይን ጥሬዕቃና ምርትን ባግባቡ ለማስቀመጥና ለስራ ምቹ ሁኔታን ያካትታል? | | | |

የፕሮጀክቱ ባለቤት፤ ስም-------------------------------------- ፊርማ--------------------------- ቀን-------------------

በግምገማው ውጤትና ባለፕሮጀክቱ በገባው ቃል መሰረት ፕሮጀክቱ እንዲተገበር ይሁንታ ይገባዋል☐/አይገባውም☐፤

ግምገማውን ያደረጉ ባለሙያዎች፤

1. ስም------------------------------------- የስራ ድርሻ -------------------------- ፊርማ ------------- ቀን ------------
2. ስም------------------------------------- የስራ ድርሻ -------------------------- ፊርማ ------------- ቀን ------------
3. ስም------------------------------------- የስራ ድርሻ -------------------------- ፊርማ ------------- ቀን ------------

# አባሪ 2

## በክ/ከተማ ፕሮጀክቶች የሚያስከትሉት አካባቢያዊ ችግሮች ሲገመገሙ ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮች

| ተ.ቁ | የፕሮጀክቱ ዓይነት | ፕሮጀክቱ የሚያስከትለው አሉታዊ ተጽዕኖዎች | በግምገማ ወቅት ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ መስፈርቶች |
|---|---|---|---|
| 1. | የወፍጮ ቤት | የድምጽ ብክለት/Noise pollution/<br>የአየር ብክለት /አዋራ/Air Pollution/<br>የደረቅ ቆሻሻ /Solid waste/<br>የአካባቢን ገጽታ የሚያበላሽ ግንባታ/nuisance pollution/<br>የሕንጻ ንቅናቄ/vibration impact/<br>የቅመማቅመምና በርበሬ ሽታ የሚፈጠረው ችግር<br>ከጋማ ከብቶች ፋንድያ የሚፈጠር የአካባቢ ብክለት(ከገጠር ጋር የተዋሰኑ ክ/ከተሞች) | ወፍጮ ቤቱ የሚገነባበት/የተገነባበት ቁሳቁስ ብሎኬት መሆኑን መረጋገጥ፣<br>ከመኖሪያ/የንግድ ቤት የጋራ ግድግዳ ያለመኖሩን መረጋገጥ ፣<br>የአቧራ መውጫ በጣሪያ ላይ ከፍ ብሎ መዘጋጀቱን ማረጋገጥ /እስከ 1 ሜትር/ ፣<br>በአካባቢው ላይ የማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ያለመኖራቸውንን ማረጋገጥ ፣ /የትምህርት የጤና የሕጻናት ማቆያ/<br>ሌሎች የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ያለመኖራቸውን ማረጋገጥ ፣<br>የቅመማ ቅመምና በርበሬ ወፍጮ ከመኖሪያ ሰፈር በጣም መራቅ አለበት፡፡ |
| 2. | የፎቶ ስቱዲዮ | ከማተሚያ ቀለም የሚወጣው አደገኛ ኬሚካል<br>ደረቅ ቆሻሻ/ወረቀት/ | ከማተሚያ ቀለም /Toner/ የሚወጣው አደገኛ ኬሚካል የሚወገድበትን ዘዴ በግልጽ ማስቀመጡን ማረጋገጥ ፣<br>የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ዘዴን መፈተሽ ፣<br>የፎቶ ስቱዲዮ በማንኛውም ቦታ ሊገነባ ይቻላል፡፡ |
| 3. | የሙዚቃ ቤት/ካሴት ማከራያ፣ ማከፋፈያ/ | የድምጽ ብክለት/ Noise pollution/<br>ንዝረት /vibration/ | በመኖሪያ መንደሮች ውስጥ ያለመሆኑ ፣<br>የድምጽ መጠኑ በተቀመጠለት ስታንዳርድ እንደሚሰራ ማረጋገጥ፣<br>ማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ማለትም /ት/ቤት ፣ የሕጻናት ማቆያና መማሪያ ፣ የህክምና መስጫ ፣መንግስታዊና መ.ያ.ድ ተቋማት በአካባቢ ያለመኖራቸውን ማረጋገጥ፣ |

| ተ.ቁ | የፕሮጀክቱ ዓይነት | ፕሮጀክቱ የሚያስከትለው አሉታዊ ተጽዕኖዎች | በግምገማ ወቅት ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ መስፈርቶች |
|---|---|---|---|
| 4. | የምሽት ክበብ | የድምጽ ብክለት / Noise pollution/<br>የአየር ብክለት መታፈን /soffocation/<br>የእሳት አደጋ /fire hazard/<br>ባህላዊ ተፅዕኖዎች | በቂ የአየር ዝውውር መኖሩን ማረጋገጥ /መስኮት፣ ቬንትሌተር የአየር ማቀዝቀዥያ<br>ቤቱ ድምጽ ወደ ውጪ የማያስወጣ መሆኑን ማረጋገጥ፣/sound proof/<br>ከመኖሪያ ሰፈር፣የሕክምናና ትምህርት መስጫ ተቋማት የእንግዳ ማረፊያ፣ በአካባቢ ያለመኖራቸውን ማረጋገጥ ፣<br>በቂ የተሽከርካ ማቆሚያ /Parking/<br>መኖሩን ማረጋገጥ ፣ /ከመንገዱ በተጨማሪ/<br>በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የወጣውን የድምጽ ስታንዳርድ የሚያሟላ መሆኑን ማረጋገጥ፣ |
| 5. | ዳቦና ብስኩት መጋገሪያ | ከፍተኛ ሙቀት /Thermal Pollution/<br>የእሳት አደጋ /Fire Hazard/<br>ፍሳሽ ቆሻሻ /Liquid waste/<br>ደረቅ ቆሻሻ /solid waste/<br>የድምጽ ብክለት/ከማቡኪያ ማሽኑ የሚፈጠር/<br>የአየር ብክለት/ከጭስ/<br>አላስፈላጊ ሽታ/nuisance smell/ | ዳቦ ቤቱ የተገነባበት ማቴሪያል ከብሎኬት መሆኑን ማረጋገጥ<br>የእሳት ማጥፊያ /Fire extingusher/ መኖሩን ማረጋገጥ፣<br>ከመኖሪያ /የንግድ ቤት ጋር የጋራ ግድግዳ ያለመኖሩ፣<br>ለሚጠቀሙበት እንጨት መከማቻ ቤት ቦታ መኖሩ ፣<br>ፍሳሹን የሚጠራቅምበት ማከማቻ /Septictank መኖሩን ማረጋገጥ ፣<br>ለደረቅ ቆሻሻ ማከመቻ በቂ ቦታ መኖሩን ማረጋገጥ ፣<br>የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ስርዓቱን መፈተሽ ፣<br>የእሳት አደጋ ተሽከርካሪ ማስገባት መቻሉን ማረጋገጥ<br>የማቡኪያ ድምጽ በደረጃ መሆኑን ማረጋገጥ፣<br>መጋገሪያ ማሽኑ በኤሌክትሪክ የሚሰራ መሆኑን ማረጋገጥ፣<br>መጋገሪያው ከሸክላላ ጡብ መሆኑን ማረጋገጥ<br>ማድበልበያው ከአልሙኒየም ፣ከወጥ ጣውላ ወይም ከእምነበረድ መሆኑን ማረጋገጥ፣ |
| 6. | የልብስ እጥበት /Laundry/ | ፍሳሽ ቆሻሻ /አደገኛ ኬሚካል | በፍሳሽ ቆሻሻና አደገኛ ኬሚካል መከማቻ የሚሆን ማጠራቀሚያ /septic tank/ መኖሩን ማረጋገጥ፣ |
| 7. | አነስተኛ የምግብ ዘይት መጭመቂያ | ደረቅ ቆሻሻ /ፋጉሎ/<br>ፍሳሽ ቆሻሻ / liquid waste/<br>አላስፈላጊ ሽታ/nuisance smell/<br>የማሽኑ ድምጽ/Noise pollution/<br>የአየር ብክለት/ከጭስና አቧራ/ | ዘይት መጭመቂያ የራሱ የሆነ ግቢ ሊኖረው እንደሚገባ ማረጋገጥ ፣<br>በቂ የፍሳሽ ማጠራቂሚያ /septictank/ መኖሩን ማረጋገጥ፣<br>በፋጉሎ ማካመቻ የሚሆን በቂ ቦታ መዘጋጀቱን ማረጋገጥ፣<br>የፍጉሎ አወጋገድ ስርዓቱ ምን እንደሚመስል መገምገም ፣<br>ሽታውን ለማስወገድ የሚጠቀምበት ዘዴ ግምት ውስጥ ማስገባት፣<br>ጥሬ እቃው ሲበጠር የሚውጣውን ብናኝ/አቧራ/ በአግባቡ መቆጣጠር ፣ |
| 8. | ጋራዥ የመኪና እጥበትና ሌሎች ከጋራዥ ጋር | ከጋራዥና የመኪና እጥበት የሚፈጠረው ፍሳሽ ቆሻሻ ከብየዳ የሚነሳ የጨረር ብክለት | በአካባቢው የአገልግሎት መስጫ ተቋማት ት/ቤት የጤና ተቋም የመንግስትና መያድ ተቋማት ያለመኖራቸውን ማረጋገጥ፣ |

| ተ.ቁ | የፕሮጀክቱ ዓይነት | ፕሮጀክቱ የሚያስከትለው አሉታዊ ተጽዕኖዎች | በግምገማ ወቅት ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ መስፈርቶች |
|---|---|---|---|
| | ተያያዥነት ያላቸው ስራዎች | ከቅጥቀጣና ብየዳ የሚፈጠር የድምጽ ብክለት<br>ከግሪስና ከሌሎች ፍሳሾች ምክንያት የሚፈጠር የአፈር ብክለት<br>ደረቅ ቆሻሻ/የብረት ቁርጥራጮች…./<br>አደገኛ ኬሚካሎች/የመኪና ዘይት ፣ባትሪ፣ ቀለም…./ | ለፍሳሽ ማጠራቀሚያ የሚያገለግል በኮንክሪት የተሰራ ማጠራቀሚያ /septic tank/መኖሩን ማረጋገጥ ፣<br>ለመኪና እጥበት የሚውለው ውሃ በአግባቡ ተጣርቶ ወደ ውሃ አካላት ሊያስገባ የሚችል ግንባታ መኖሩን ማረጋገጥ፣<br>ጋራዥ የራሱ የቻለና በቂ ግቢ እንዳለው ማረጋገጥ፣<br>ከግቢ ውጪ መኪናዎችን በማቆም አከባቢን እንደማይበክል ማረጋገጥ፣<br>ከማንኛቸውም የመኖሪያ ቤቶች ጋር የጋራ ግድግዳ እንደሌለው መረጋገጥ፣<br>በአካባቢ ላይ ሊፈጠር የሚችለውን የጨረር ብክለት ለመቀነስ እንዲቻል በየዳ በሚካሄድበት አካባቢ ላይ በቂ መጠለያ መኖሩን ማረጋገጥ፣<br>ድምጽ በአካባቢ ያሉትን ተቋማትና ነዋሪዎች እንዳይረብሽ ሰፊ ግቢና ከተቋማት የራቀ መሆኑን ማረጋገጥ፣<br>የስራ ቦታው ወለል በኮንክሪት የተገነባና መጠለያ/shade /ያለው መሆኑን መረጋገጥ፣<br>የቀለም መቀባቱ ሂደት/spray /በተወሰነና በተከለለ ቦታ በጥንቃቄ መካሄድ እንዳለበት ማረጋገጥ፣<br>በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የወጣውን የድምጽ ስታንዳርድ ማሟላት፣ |
| 9. | መለስተኛ የጤና ተቋማት ጤና ጣቢያ መለስተኛ ክሊኒክ | ታማሚ ሰው ከተጠቀመባቸው ቁሳቁሶች የሚፈጠር የኢንፌክሽን በሽታ /ከመርፌ፣ ከጥጥና ፋሻ የሚከሰት/<br>የፍሳሽ ቆሻሻ<br>የደረቅ ቆሻሻ<br>ሌሎች ባዮሜድካል ቆሻሻዎች/የሰውነት ክፍሎች…/ | በሽተኛ የተጠቀመባቸውን ቁሳቁሶች እንደገና ለመጠቀም እንዲቻል ተቋሙ የአውቶ ክሌብ ማሽን ሊኖረው ይገባል<br>በሽተኞች የተጥቀሙበትን ቆሻሻና ሌሎች የሚፈጠሩ ደረቅ ቆሻሻዎችን ለማስወገድ እንዲችል በጡብ የተገነባ ማቃጠያ/Incinerator/ ሊኖረው ይገባል፡፡<br>የማቃጠያው ጭስ ማውጫ /smoke stack/ ከ3-6 ሜትር ርዝመት ሊኖረው ይገባል፡፡<br>የሚፈጠሩትን ፍሳሽ ቆሻሻ ለማስተናገድ የሚችል በኮንክሪት የተሰራ የፍሳሽ ማጠራቀሚያ /septic tank/ ሊኖረው ይገባል፡፡<br>የጤና ተቋሙ እራሱን በቻለ ግቢ ሆኖ ከመኖሪያ፣ከምግብ፣ከሻይ ቤቶችና ከመሳሰሉት ያልተያያዘ መሆኑን ማረጋገጥ፣<br>የጤና ተቋሙ በቂ ብርሃንና አየር ማስገቢያ ሊኖረው ይገባል፡፡<br>የማዋለድ ስራ የሚሰሩ ከሆነ የእንግዴ ልጅ መቅበሪያ /placenta pit/ መኖሩን ማረጋገጥ፣<br>ንጽሕና የተጠበቀ መጸዳጃ ቤት፣ የእጅ መታጠቢያና የቆሻሻ መጠራቀሚያ መኖሩን ማረጋገጥ፤ |

| ተ.ቁ | የፐሮጀክቱ ዓይነት | ፐሮጀክቱ የሚያስከትለው አሉታዊ ተጽዕኖዎች | በግምገማ ወቅት ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ መስፈርቶች |
|---|---|---|---|
| 10. | የቤት ውስጥ ምግብ ማቀነባበር ማሽኒያ | ለእቃና ጥሬ እቃ ማጠቢያ የሚያገለግል ፍሳሽ በአካባቢ ላይ የሚፈጥረው ችግር<br>የደረቅ ቆሻሻ አላስፈላጊ ሽታ /nuisance smell/<br>በቂ ብርሃንና የአየር ዝውውር ያለመኖር<br>የድምጽ ብክለት<br>ጭስ | ለማቀነባበሪያው ማሽኒያ የሚያገለግለው ቤት የራሱ የቻለ ግቢ ሊኖረው ይገባል፡፡<br>የሚፈጠረው ፍሳሽ ቆሻሻ ለማጠራቀም የሚችል በቂ ስፋት ያለው ማጠራቀሚያ /septic tank// ሊኖረው ይገባል፡፡<br>ደረቅ ቆሻሻን ለማከማቸት የሚያስችል በቂ ማከማቻ መኖሩን ማረጋገጥ፣<br>ለጥሬ እቃና ያለቀለትን ምርት ለማከማቸት የሚችል በቂ ቦታ መኖሩን ማረጋገጥ፣<br>በሚሰራበት ቤት ውስጥ በቂ ብርሃንና የአየር ዝውውር መኖሩን ማረጋገጥ፣ ጭስ ማውጫ |
| 11. | አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች፣ የእንጨት የብረታ ብረትና የመስታወት ስራዎች | የእንጨት ፣የብረታ ብረትና የመስታወት ቁርጥራጮች ምክንያት የሚፈጠር ደረቅ ቆሻሻ<br>በእንጨት ስራ ምክንያት የሚፈጠር ብናኝ<br>የሚያስከትለው የአየር ብክለት<br>ከእንጨትና ብረት ማሽኖች ምክንያት የሚፈጠር የድምጽ ብክለት<br>በቂ ብርሃን ካለመኖር ጋር የሚፈጠር ድንገተኛ አደጋ<br>የሰራተኞች ጉዳት/accident or mechanical injuries/ | የማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማትና ሌሎች የመንግስትና መ.ያ.ድ ጽ/ቤቶች በአካባቢው ያለመኖራቸውን ማረጋገጥ፣<br>ካፌዎች፣ሆቴሎችና ሌሎች የመዝናኛ ማዕከሎች በአካባቢ በበቂ ርቀት መኖራቸውን ማረጋገጥ ፣<br>ከማሽን የሚፈጠረው ድምጽ አምቆ ለመያዝ የሚያስችል ግንባታ መኖሩን ማረጋገጥ ፣<br>በቂ የብናኝና ደረቅ ቆሻሻ ማከመቻ ስፍራ መኖሩን ማረጋገጥ<br>በቂ ብርሃንና የአየር ዝውውር መኖሩን ማረጋገጥ ፣<br>አቧራ/ብናኝ/ ማውጫ የሚሆን ግንባታ በጣሪያው ላይ መኖሩን ማረጋገጥ፣<br>ለአካባቢው የሚመጥን የድምጽ ደረጃ መኖሩን ማረጋገጥ፣<br>ቀለም ሲቀባ በጥንቃቄ መሆኑን ማረጋገጥ፣<br>ለሰራተኞች አስፈላገወ የስራ ላይ አደጋ መከላከያ ቁሳቁሶች ማሟላታቸውን ማረጋገጥ፣ |
